

# ከአንበሳ መንጋጋ ማን ይቀማል ሥጋ(1

*

ከአንበሳ መንጋጋ፣ ሥጋ ማን ይቀማል

እንዴት ይገባኛል የሚል ሰው ይጠፋል፣

ታማኝ ፈረስ መሆን የትስ ያደርሰናል፣

ፍስሃም የለውም እንዴት ያሻግራል፣

ብርሃኑም ጠፍቷል ግራ ተጋብተናል፤

***ጋብቻው ግን ቀርቧል!***

ኢትዮጵያን እስከንድር፣ አዎ እንጠብቃለን
በዚችኛዋ ምድር፣ መንፈስ ጠንክሮልን፣
የነገን ለነገ ባንዱ ዓለም እየኖርን፣
የዛሬም አዳር ነው፣ እስከዚያውስ ቢሆን፤

አራምባ ና ቆቦ ምን ያራግጠናል፤

***ምነው ደፋር ይጥፋ የሚል ይገባኛል?***

ጀንበሯም ጠለቀች አርባ ዓመት ስናዘግም
በማናውቀው ሸንጎም ሳናድግ ሳንጠራም
በማንትስ ጉያ „ ነጻ አውጪ“ ም አንሻም፤
ከንግዲህስ በቃን ባዕድ ኳስ አንሆንም።
እንደ መላ፥ቢሱም፣ አንቆሻሽም፤
ደምም አንገብርም
አውራም አንገልም።

አውራውማ ሄዷል ሸከሙም ተቃሏል

ከህግ ውጭ ሥራ፣ ላኛው ገላግሎናል፣

መንጋው ብቻ ተርፎ ይተረማመሳል፤

***ለየት የሚያደርገው መላ ሰጪ አጥቷል፣***

***ማሰብ የሚችል ሰው፣ የሚመራው ጠፍቷል።***

ጥንትማ አጥንት ነው
ያለነው ዛሬ ነው፣
ዘመን ተሃድሶ፣ ይልቅ የሚበጀው፥
***እጅ ተያይዞ ፣ ለየት ባለው መንጋ፣***
***አዋቂው ሲንጋጋ***
***እንዳማኙ ነቢይ፣ ለመብት የሚዋጋ፣***
***ሞትን ያሸነፈ ለሞት የማይሰጋ***
***የነፍሱ ባለቤት ሳያድር ለስጋ፣***

*ባሻንጉሊት ፓፓስ በተንኮል ቢወጋ፣*

*አሻፈረኝ ያለው ክርስቲያን ሲተጋ*

***ያን ማዶን ጎበኝቶ፣ ል ብ፥ያ ለ ው - የረጋ፣***

***ይገባኛል ሲል ነው፣ የሚገኘው አልጋ !***

***ይገባኛል ብሎ ይገባዋል ሲባል፣***

***ወዳጅ ሰው ልብ ይበል***

***ያ ኔ ለውጥ አነዣቧል፣ ጋብቻው ይሆናል ።***

***>>>>>>***

---

(1 *እነዚህ መስመሮች ብቅ ያሉት፣ ደፋር ሰውና አንድ የኀበዝ የሰው ቡድን፣ እንዴት ብልህነት ጨምሮበት ካንበሳ መንጋ ስጋ እንደሚወስድ የሚያሳይ ቁራጭ ፊልም አይቼ ሳደንቅና፣ በለውጥ ሂደቶች ታሪክ ውስጥ፣ ለክፉም ሆነ ለደግ፣ የሁሉም የለውጥ ዓይነቶችን፣ የጋራ የሆነውን ቁም ነገር ሳስታውስ ነው። ሴዛር፣ አሌክሳንደር ቢባል ናፖልዮን፣ ሌኒን ማኦ ስታሊን ቢሉት ሞሶሎኒ ፍራንኮና ሂትለር፣ አጼዎች ቴዎድሮስ፣ ዮሃንስ ሚኒሊክ፣ ቢታወሱ ጃንሆይ፣ ቢነሳ መንግሥቱ፥ ቢጠራ መለሰ፣* ***አልፎም እንደጋንዲ፣ ከሆነም ማንዴላ፣*** *የየለውጡ ዓይነቶች ሁሉ፣ ለደግ ሆነ ክፉ፣ አልጋ ፈላጊዎች ያላቸው የጋራ ጉዳይ፣ ይገባኛል ሲሉ ሁሉም መቁረጣቸው ነው!*

*ይህ የሌለበት ለውጥ በታሪክ ውስጥ መከሰቱን እጠራጠራለሁ!*

http://www.youtube.com/watch?v=Z3AtVgiYKd8&feature=youtu.be